# የአዳም ሣልሳዊ መና "ከሰማይ የወረደ ፍርፍር"

**ሶፎኒያስ አቢስ? (አዲስ አድማስ)**

አዳም ተመልሶ መጥቷል የአሁኑ ሣልሳዊ አመጣጥ ነው፡፡

ሣልሳዊነቱ በአጭር ልብወለድ መድብል ነው፡፡ በ1981 በኩራዝ አሳታሚ የታተመው "ማህሌት" እና በ2001 በማህሌት አሳታሚ የታተመው "አለንጋና ምስር" ቀዳማይ እና ተከታይ ናቸው፡፡

በዚህ ጽሁፍ መጠነኛ ዳሰሳ የምናደርግበት መጋቢት 2002 ዓ.ም በማህሌት አሳታሚነት ለንባብ የበቃው "ከሰማይ የወረደ ፍርፍር" ደግሞ ሣልሳዊ በረከት፡፡

ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ይሄ ሣልሳዊነት የእሱ አጫጭር ልቦለዶች ብቻ ባካተቱ መጽሐፍት ቆጠራ ማዕከልነት የተነገረ ነው፡፡

ከተደራሲው ጋር በመንፈስ ዕውቂያ፤ እንዲሁም ምናባዊ መጨባበጥ ያደረገበት እና በኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍ ተከታታዮች አንባቢዎች ልብ ውስጥ የመሰረት ድንጋይ ያስቀመጠበት "አባ ደፋር እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች" በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት የታተመው በ1977 ዓ.ም ነው፡፡ (በዚህ መድብል ውስጥ አራት ሥራዎችን አዋጥቷል፤ "ድብድብ"፤ "ዕብዱ ሺበሺ"፤ "ሲሮኮ" እና "ሲፊንክስ")፡፡

ሜጋ አሳታሚ ድርጅት በ1999 ዓ.ም ባሳተመው "ጭጋግና ጠል" የአጭር ታሪኮች ስብስብ "ዘላን" የተባለው ልቦለዱ ታትሟል፡፡

እነዚህ ሁለቱ ከሌሎች ደራሲዎች ሥራዎች ጋር የታተሙለት ስለሆነ እንደ ወጥ ሳይቆጠሩ ነው ከላይ የሰፈረው የተባለው፡፡

ዝርያቸው(Gener) የተለየ በመሆኑ ያልተቆጠሩት በ1997 ዓ.ም በሻማ ቡክስ የታተመው ብሉይ(Classsic) ስራ "ግራጫ ቃጭሎች" (ረጅም ልቦለድ ነው) እና በ2001 ዓ.ም የታተመው በቅርጽ ፍጽም የተለየና ቤሳ ልቦለዶችን (ኖቬላ) የያዘው "እቴሜቴ ሎሚ ሽታ" ሲቆጠሩ ያሁኑ አምስተኛ ዙር ይሆናል፡፡

በነገራችን ላይ "እቴሜቴ ሎሚ ሽታ" እጅግ ጥቃቅን በሆኑ የድርጊት ድሮችና በጣም ቀጫጭን በሆኑ የታሪክ ክሮች ልቦለዶቹን ሊያያይዝ የሞከረበት በመሆኑ፤ በጥቂቱም ቢሆን ረጅም ልብወለዳዊነት (ኖቭልነት) የሚታይበት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ታዲያ አዳም ዘንድሮም ለመምጣት ብቻ አልመጣም፡፡ ወይም በደራሲ የመነበብ ናፍቆት ተገፍትሮ፡፡ ይልቁኑ የልብ ወለድ ምድረ በዳ እየሆነ ያለ የሚመስለውን የጥበብ መስክ ሊያለመልም ይመስላል፡፡ በድሮ በሬ እያረሰ የዘንድሮውን ማሳ ሊያሳምር፡፡

አንዳንዴ ያጠረ አንዳንዴ የሳሳ፤ አንዳንዴም ሌላ መልክ ያዳቀለ ሌላ ወዝ የጨመረ ይምሰል እንጂ አሻራው ግን እንደነበረ አለ፡፡ በዚህ በ"ከሰማይ የወረደ ፍርፍር" የመጣው አዳም ያው አዳም ደራሲው ነው፡፡ አሁንም የቋንቋ ጌትነቱ እንዳለ ነው፡፡ አሁንም የገለፃዎች ሽማኔ ነው፡፡

ካለው ነገር የሌለውን የሚያፈልቀው አብራኩ አልላመም፡፡ በሁሉም የሚታይ ግን በብዙዎች የማያስተዋሉ የሕይወት ደቃቅ ገጽታዎችን አግዝፎ የማኅበራዊ ህይወትን መልክና ዘርፈ ብዙ ውጥንቅጥ አንጥሮ እና ኳኩሎ የሚወልደው ማህፀኑ አላረጠም፡፡

አሁንም እንደ ኢትዮጵያዊው ደራሲና የቋንቋ ሊቅ ዳኛቸው ወርቁ በአማርኛ ቋንቋ ላይ እንደ ልቡ ተራቋል፡፡

አሁንም እንደ ሩሲያዊው ደራሲ ፊይዶር ዶስቶቭስኪ የስነ ልቦና ምስቅልቅል እና ውስጣዊ ቀውስን በጥልቀት ዳስሷል፡፡

አሁንም እንደ ሩሲያዊው የአጫጭር ልቦለዶች አምራች አንቶን ቼኮቭ አነስተኛ የሚመስሉ ግን ያይደሉ የጎዳና የድህነት ጣጣዎችን ተርኳል፡፡

የቅርፅ(Form) ፍቅሩም ቢሆን እንደ ወትሮው ጎልቶ ይታያል፡፡

መልከዓ ምድርና ትዕይንቶችን አግዝፈውና አፍክተው የሚያሳዩት ገለፃዎቹ ውበትና ለዛቸው እያፈዘዘን ወደ እኛ ወደ ተደራሲዎቹ ዓይንና ልብ ይሰጥማሉ፡፡

“...ጡቶቿ የላሉ ጠይም ማንጎዎች ናቸው፣ የአርሲ ፀሀይ እንደተቆጣቻቸው ... ረዣዥም ጣቶቿ ሥር እንደ ሐር ቀረጢቶች ያደርጋቸዋል፤ ውስጣቸው ያልበረደ ፍትወት ያጋቱ፡፡ ድምቶቹ እንደሚበላሉ ሁሉ ወፍራምና ቀጭን የተጎነጉኑ ድምጾች ወደየትም ይልካሉ... ገርበብ ባለው መስኮት ያልረካ የወሲብ ቁጣ ሳያፍር ይገባል... በአብራክ በኩል ዘሎ ሊወጣ እከኩን የሚነሰንስ፡፡ ከትከሻዎቿ ወዲያና ወዲያ ጨለማ ነው ከመሀላቸው በደረቷና በእግሮቿ መሀል ብቸኝነቷን የሚገስ የሙብረቅ ብልጭታ፡፡...

...ብርማ ጭኖቿ መሐል የምታዛጋ ቁንጮ... (የሚያንጸባርቅ ጥርስ ገጽ 49)

ሌላ ምሳሌ ልጨምር

“... ያ ጓደኛዬ ዋና ገፀ ባህሪይ አድርጎ የፈጠረው ሰው ሚስቱ ላይ እንዴት እንዲቀልድባት ነው ያደረገው?

ሴት እንደ ጡቷ ናት<br>
በባሏ ትታሻለች<br>
በልጆቿ ትጠባለች...” (ገጽ 47)

የሚገርም እይታ፡፡ የሚገርም ገለፃ (በተለይ ለዛ ዘመን)፡፡ እያሳቀ የሚያሳምም፡፡ እያሳመመ የሚያስፈግግ ባለመንታ ስለት ቋንቋ፡፡ ጣትና ጨቤ፣ ኮርኳሪና ወጊ ሳቅ፣ እንባ፡፡ እንባ፣ ሳቅ...
አዳም በዚህ መጽሐፍ ያካተታቸው 14 ታሪኮች ከ1976 እስከ 1988 በተዘረጋ የጊዜ ሐዲድ ላይ በተለያዩ ፎርማታዎች የተፃፉ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ፎርማታ 1976 የመጨረሻው 1988 በ“ከሰማይ የወረደ ፍርፍር”ም አዳም ወደ ኋላ መመለሱን ቀጥሏል፡፡ ልጅነትን ማዕከል ያደረጉ ታሪኮቹን ለንባብ መብቃታቸው ዛሬም ገና አላበቃም፡፡

አራቱ ታሪኮች (ለብሮት፣ ትርንጎና ገብረ ጉንዳን፣ ኡሪዎች፣ ትንቢተ ቁራ) ልጅነት ተኮሮችና የልጅነት ሕይወት የሚተረክባቸው ናቸው፡፡

አብዛኞቹ የአዳም ገፀባህሪያት ታዲያ እንደ ልጅ የሚኖሩና እንደ ልጅ የሚናገሩ አይደሉም፡፡ ብስል ልጆች ናቸው፡፡ ቋንቋቸው አማርኛ ሳይሆን አዳምኛ ነው፡፡ ደራሲው የቋንቋውን ኮስታራነት የገለፃዎቹን ሸንጣምነትና በሀሳቦች የበለፀጉ መሆን ላለማጣት ሲል ልጆቹን በልጅነት ዕድሜና አዕምሮ አይቀርጻቸውም፡፡ ከጉልምስና በትውስታ ወደ ኋላ ይወስዳቸዋል፡፡ በአዋቂና ሊቅ ቋንቋና ገለፃ ልጅነትንና የልጅነት ገጠመኞቻቸውን ያስተርካቸዋል፡፡

በ“ከሰማይ የወረደ ፍርፍር” ከታተመሙት አራቱ ታሪኮች ሶስቱ በዚህ ስልት (ቴክኒክ) የቀረቡ ናቸው፡፡ እንደ እንዳለ ጌታ ከበደና እንደ ሌሎችም አይተርካቸውም እንጂ (በተለይ በአንደኛ መደብ ተራኪ በሚተርኩት) የገፀ ባህሪያቱ ድርጊቶች ግን የልጆች ናቸው፡፡

አንዳንድ ትዕይንቶችም የልጅነትን ስነ ልቦናና ባህሪ በሚገባ መረዳቱን የሚያሳዩ ናቸው፡፡
ከ“ትርንጎና ገብረ ጉንዳናን” አንዷት ትዕይንት እንቃኝ፤

“… አፌ ውስጥ ያለው ከረሜላ አላናገረኝም፡፡  አወጣሁት፡፡ በአመልካችና በአውራ ጣቴ መሀል ይገኙ ዝንቦች  እጄ ዙሪያ “ጥዝ” እያሉ፡፡ ሊቀመጡባት ይችሉ እንደሆነ ከረሜላውን ዝም ብዬ ያዝኩላቸው እንድዋ እጄ ላይ አረፈች፡ ወደ ክንዴ መሄድ ጀምራ ተመለሰች፤ ትንንሽ እግሮቿ ይታዩኛል… ፊቷን አዞራ ወደ ጣቶቼ መምጣት ጀመረች፡፡ እየቆመች እያጠናች፡፡ ምላሷን ቆዳዬ ላይ እየተመተመች፡፡ አውራ ጣቴ ላይ ደረሰች ብዙ ትቆማለች፡፡ ከረሜላዋ አጠገብ ደረሰች የፊት እግሯን አንስታ ቆመች፡፡

በምላሷ ከረሜላዋን እየተመተመች ከነከረሜላው ወረወርኳት በፍጥነት እንደምትነክሰኝ ያህል ፈርቼ፡፡”

በጥቂት ነገር የመደመምና ነገሮችን የመፈተን ባህሪ ያምናይባቸው ህጻናት ብዙ ናቸው፤ በዚህ ትዕይንት በእውን የማናውቃቸው ልጆች ትውስ ይሉናል፡፡

ይህን ካልኩ በኋላ በዚሁ ታሪክ ላይ ጥያቄ የሆነብኝን ነገር ላንሳ፡፡ የሚተርከው ድርጊት ሲፈፀም የ5 ዓመት ህጻን የነበረውን ተራኪ ትርንጎ (የእናቱ ጓደኛ ናት) መንገድ ላይ ታየውና ታናግረዋለች፡፡

ተራኪው ስለ እሷ ሲነግረን “ከውስጥ ቀይ እግር ይታያል የፀሐይ ብርሃን ወድቆበት፡፡ ልቤ ይመታል” (ገጽ 112) ይላል፡፡ የአምስት ዓመት ህጻን ቀይ እግር አይቶ ልቡ የሚመታበት ምክንያት ምን ይሆን? ወንድነት ተሰምቶት? ወይስ …?

በዚህ ታሪክ ውስጥ ተመሳሳይ አዝማሚያ ያላቸው ገለጻዎች ገጥመውኛል፡፡ እና ወይ የልጁ እድሜ ከፍ ማለት ነበረበት ወይ እነዚህ ገለጻዎች መቀነስ ነበረባቸው ብዬ አስቤያለሁ፡፡
አሁን ወደ ሕልማዊ (ፋንታሲ) ስራዎች እንለፍ፡፡ አዳም ለምናብና ፋንታሲ አዲስ አይደለም፡፡ በ“ማህሌት” መድብሉ አበቦችን ሊያናግር ሞክሯል፡፡ ከታሪኩ ጋር ብዙ የሚያያዝ ባይሆንና አሳማኝ ባልሆነ መልኩ መሀል ላይ ቢሰነቀርም፤ በ“ግራጫ ቃጭሎች”ም ሕልም ወለድ ትዕይንቶችን አስነብቦናል፡፡ በተጨማሪም በ“አለንጋና ምስር” መጽሐፉ ተረት ወለድ የሆነው “የብሩክታዊት ጠጠር” እና በ“እቴሜቴ ሎሚ ሽታ” ከመጽሐፍ ቅዱስ ወደ ምናብ የሚያስወነጭፈው (Bible Fusion) “በለስ” ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ይሄ በተደጋጋሚ ደረስ መለሰና ጥረት፣ ደራሲው ለፋንታሲ ያለውን ስውር ፍቅር የሚያስረዳ ይመስለኛል፡፡

በአዲሱ መጽሐፉም ሁለት የተሳኩ ፋንታሲዎች ተካተዋል፡፡ “ዱለት፣ ጉሬና ጎሮ” እና የመጽሐፉ መጠሪያ የሆነው “ከሰማይ የወረደ ፍርፍር” ሁለቱም ድርሰቶች መነሻቸው ማህበራዊ ነው፡፡ ከመጀመሪያ እንጀምር፡፡

“ዱለት፣ ጉሬና ጎሮ” ታሪኩ የሚካሄድበት ጎዳና ሳይቀር ሕልማዊ ነው፡፡ ደራሲው “ይሄ ጎዳና የዶሮ ነው፡ በከተማ ካርታ ላይ ‘ኩኩሉ አቬንዩ’ ይባላል፡፡” ይለናል፡፡

ወረድ ብሎ “ከተማዋ ስትቆረቆር የዚህች አከባቢ ቀበሌ ስምዋን “ዶሮ ማነቂያ” ብሎ የደነገገው ምሹ ዳውድ የተባለ ኢንጂኒየር ነው ይባላል”፡፡ ሲለን ደሞ ምናባዊውን ጎዳና በ“ዶሮ ማነቂያ” አካባቢ እንደዘረጋው ይገባናል፡፡

የጎዳናው ባንዲራም የተለየ ነው፡፡ “በየመንገዱ የተንጠለጠሉት ባንዲራዎች የሚያሳዩት አስኳል የመሰለ ቢጫ ጨርቅ ላይ የተሳሉ ሁለት እንቁላሎችና ምክንያቱ ባልታወቀ ምክንያት እንቁላሎቹ መሐል ቆማ የምትስቅ የመሰለች አንዲት ዶሮ ናት፡፡ ባንዲራቸው የዶሮ ነው፡፡” (ገጽ 135)

በዓመት አንድ ጊዜ ከግንቦት አንድ እስከ ሰባት በሚከበረው “ብሔራዊ የዶሮ ቀን” የዶሮ ሰልፈኞች ሰልፍ እንደሚወጡም ይነግረናል፡፡ እና የተለየ ድባብና አካባቢ ውስጥ ይከተናል፡፡
ሕልማዊ ዳና የዶሮ ውጊያና ቁማር ያደረበት፡፡ ሕልማዊ ኑሮ በረሀብ ችጋር የቆረቆዘ፡፡
የሶስት ልጆች እናት የሆነችው ሴት የዚህ ሕልማዊ ጎዳና ነዋሪ ናት፡፡ እውናዊ የሆነች፡፡ የእናቶች ሁሉ እናታዊ ባህሪ የሚታይባት፡፡ እንቅልፍ የመፈለግ ምልክት ያየችበትን ልጇን ወደ ጉያዋ ሰብሰብ የምታደርግ፡፡

ከሰውኛ ትዕይንቶቹ በተጨማሪ የልቦለዱ ዋነኛ ማህበራዊ መነሻም ይኸው ነው፡፡ እናታዊነት፡፡ እናቲቱ ኑሮዋንና ፈጣሪዋን ታማርራለች፡፡ “እንኳኳሁ... ከብዙ ጊዜ በኋላ ...ልመና ዘላ ትወጣለች... እንኳኳሁ ... ልመና እየሳቀች ወጣች፡፡” ( ገጽ 137)

የገጠማት ወንድ ለእሷ እንደ ባል፣ ለልጆችዋ እንደ አባት የሚሆን አልሆነም መጠጥና ስካሩን ትቶ እንዲኖርና እንዲያኖር ብትመክረው አልሰማትም፡፡: ሰክሮ በመኪና ተገጨ፡፡: እንደሰከረ ሞተ፡፡ እናት መከራዋ የሚፀናው ከዚህ ወዲያ ነው፡፡ “እናት ነኝን?” ብላ ራስዋን ትጠይቃለች
ትቀጥልና “እስከዛሬ የማይኀልበትን እሱን ፈጣሪ ለመጨረሻ ልትፈትነው ... ይሄን የመራቤን ችግር የምዋጋ ዶሮ ብሆን” እያለች ታስባለች፡፡ እነሆም ፈጣሪ “ፈተናውን” ያልፋል፡፡

ስታስብ አዕምሮዋን ጎርጉሮ ደራሲው ሀሳብዋን ሊያስነብበን የምናውቃት እንጂ ስትናገር የማናዳምጣት እናት፣ ዓይኖቻቸውን በጨፈኑ ሦስት ልጆችዋ እንደተከበበች ዓይኖችዋን ጨፍና ትፀልያለች፡፡

“እም እም ም”
ትርጉሙ ፀሎት እንደኾነ የገባቸው ልጆቿ ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው፣
“አሜን”
“እህ እህ እህ”
ልጆቿ
“አሜን”
“ዶሮ አርገኝ ላባ አልብሰኝ፣ ኩንቢ ስጠኝ፣ እም እም እም”
“አሜን”
“ከፊት ለፊቴ ካለ ሰንበቴ ቤት በርሬ ገብቼ ቂጣ መሰብሰብ ብችል” (ገጽ 140)

እልም ያለው ፋንታሲ የሚጀምረው አሁን ነው፡፡ ታሪኩ እዚህና እዚያ ሄድ መለስ እያለ ዘጠኝ ያህል ገጾችን ከዘገመ በኋላ በዐሥረኛው ገጽ ላይ እናቲቱ ወደ ዶሮ ተለወጠች፡፡

... ሌላኛው ሕልማዊ ልብ ወለድ “ከሰማይ የወረደ ፍርፍር” ነው፡፡ ይሄ ልብወለድ በተረትና ወሬ በሰማው ሰማያዊ ፍርፍር ማልሎ፣ “ከሰማይ የወረደውን ፍርፍር” ፍለጋ ሚስቱን ጥሎ ጉዞ በሚጀምር፣ እንደ ሰርቫንቴስ ፈጠራ ዶን ኪሆቴ ጀብደኛ በሚመስል ገፀ ባህሪ ዙርያ የሚያጠነጥን ነው፡፡

እንደ እዮብ ታጋሽ እና እንደ ያዕቆብ የመጠበቅ ጽናት የተቸራት፣ ታማኝነና አፍቃሪ ሚስት ባለቤት የሆነ ገፀ ባህሪ፡፡

“ከሰማይ የወረደ ፍርፍር” ን ፍለጋ ተንከራቶ ተንከራቶ አጥቶ የሚመለስ፡፡ ተመልሶ የፈለገውን ፍርፍር ቤቱ የሚያገኝ፡፡

“ፍርፍሩን” ፍለጋ ከአንዱ ወደ አንዱ ሲጠቀምና ሲዟዟር፣ ከጌዶው አዛውንት፣ ከተራራው፣ ከዝሆኑ... ቀጥሎ ያገኛቸው አሮጊት አሉ፡፡ ከሰማይ የወረደውን ፍርፍር የሠራሁት እኔ ነኝ፡፡ የመጀመሪያ ስሜ ሌላ ነው፣ ሰማይ ቤት የወጣልኝ ስም ግን ኩርሲ ነው የሚሉ፡፡

ሞቼ ተነሳሁ ባይ እኔን በመርዝ የገደለችኝ የራሴ እህት ናት ብለው የሚናገሩ፡፡

እኚህ ሴት በታሪኩ ማለቂያ ላይ ተመልሰው ይከሰታሉ፡፡ ሚስቱን ማከዳን ሆነው ወይም ሚስቱ ማከዳ እሳቸው የነገሩትን ታሪካቸውን መሰላና ሆና፡፡

ትሞታለችም፡፡ የእህቷን ቤት ጠበል ጠጥታ፡፡ ከጠበሉ ጋር መርዟን፡፡

ታዲያ ታሪኩ የሚያበቃው ዋና ገፀባህሪ ማከዳን ወይም ኩርሲን ፍሊጋ ሲነሳ ነው፡፡

ማከዳ ከመሞትዋ በፊት ዝላ ነበር፡፡ “ልብወለድ ነው ሁሉም” ይሄ ግን ዳሰሳ፡፡

በተረፈ የጎዳግ ማስታወሻዎቹ ተጨማሪ መረጃ የሚሰጡና አዝናኝ ናቸው፡፡ በልብ ወለዳዊነታቸውና በእውነተኛ መረጃዎች መሀል ግን የተሰመረ መስመር ወይም የተበጀ ኬላ የለም፡ ይሄ አንባቢን ስለሚያምታታ ቢታሰብበት መልካም ነው፡፡